# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የትምህርት ሚኒስቴር

የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ  ትምህርት ዘርፍ

## ትምህርት ለብርሃን ምዘና ማስፈጸሚያ ማኑዋል

ትምህርት ሚኒስቴር

ጥቅምት **2013** ዓ.ም

**ማውጫ** **ገጽ**

በአገራችን በተደረጉ ምርምሮች እንደተረጋገጠው እጅግ ብዙ በመሃይምነት የተፈረጁ ወይም በመደበኛው የመሰረታዊ ትምህርት መርሃ ግብሮች ተሳትፎ ያልነበራቸው ጎልማሶች በራሳቸው ጥረት ወይም በሌሎች እገዛ ሃይማኖታዊ መጽሃፍትን እንደሚያነቡ ፡ የተለያዩ ምልክቶችን በመጠቀም ማስታወሻ እንደሚይዙ ፤ በንግድ ስራ ተሰማርተው በራሳቸው መንገድ ወጪ ገቢያቸውን እንደሚያሰሉና ሌሎችም ከመሰረታዊ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን በእለት ከእለት ኑሮዋቸው እንደሚከውኑ ይታወቃል። እነዚህ ጎልማሶች በተለምዷዊ አጠራር መሃይማን በመባል ሲፈረጁ ቆይተዋል። በዚህም ምክንያት በጎልማሶች ትምህርት መርሃ ግብሮቻችን የምናተኩርባቸው ይዘቶች በበቂ መጠን የመሰረታዊ ትምህርትን ብዝሃነት እንደ መነሻም ይሁን እንደ መድረሻ ማካተት አለመቻላቸውና ጎልማሶች ከህይወትና ከሙያቸው ጋር አያይዘው የሚያውቋቸው የተለያዩ መሰረታዊ ትምህርቶች/የተግባቦት መንገዶች እንደ ትምህርት ባለመወሰዳቸው እንደመሀይም በመቆጠራቸው በመሰረታዊ ትምህርት ምጣነ መረጃ ሲያዛባ ቆይቷል። በተጨማሪም በኢመደበኛ መንገድ የመሰረታዊ ትምህርት የቀሰሙ ሰዎች ተገቢውን ምዘና ባለማግኘታቸው ቀጣይ ለሆነ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ተጠቃሚ መሆን ያልቻሉ ከመሆናቸውም በላይ አማካኝ የትምህርት እድሜ (Average year of schooling) እና በአገሪቱ የተማሩ ሰዎች ቋት (National Literacy Account) ውስጥ መካተት አልቻሉም። አገራችን ኢትዮጵያ ከዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች በንጽጽር ዝቅተኛ የተማረ የሰው ሀይል( Literacy Rate ) እንዲኖራት ካደረጉ ምክንያቶች መካከል የመሰረታዊ ትምህርት ግንዛቤያችንና ምዘና ስልታችን አስተዋጽዖ አድርጓል።

ስለዚህ በጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተሳተፉና በተለያየ መንገድ ማንበብ፤መጻፍ እና ማስላት የቻሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን "ትምህርት ለብርሀን' የሚል ምዘና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በመስጠት የወጣቶችንና ጎልማሶችን የማንበብ፤የመጻፍና የማስላት የብቃት ክህሎት ምዘናይካሄዳል።ተመዛኖች ባገኙት ውጤት መሰረት ዕውቅና እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪም የአገሪቱ አማካኝ የትምህርት እድሜና የተማረ የሰው ሀይል ቋት ማሳደግ/literacy account/ ያስችላል። ስለሆነም ይህን የትምህርት ለብርሀን ምዘና ማስተግበሪያ ማኑዋል ተዘጋጅቷል ። በመሆኑም በዚህ ሰነድ ውስጥ የማኑዋሉ አስፈላጊነት ፣ የማኑዋሉ ዓላማዎች፣ ተማዛኞች፣ የምዘናው ይዘትና አይነት፣ ምዘናው የሚሰጥበት ቦታና ጊዜ፣ የምዘና አሰጣጥ ፣ የምስክር ወረቀት፣የሽግግር ሂደት፣ የባለድረሻ አካለትና ክትትልና ድጋፍ የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተብራርተው ቀርበዋል።

## 2. የመሰረታዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ታሪካዊ ዳራ

እ.አ.አ. ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ ዩኔስኮ በመሰረተ ትምህርት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ያስቻሉት ሁለት ጉዳዮች መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። የመጀመሪያው ምክንያት “ማይምነት (ማንበብና መፃፍ አለመቻል) ለልማት ዋንኛው መሰናክል ነው“ የሚል እሳቤ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ “መሰረተ ትምህርት (ማንበብና መፃፍ መማር) ሰብአዊ መብት ነው“ የሚል እምነት ነው። ዓለምአቀፋዊ የመሰረተ ትምህርት ከ1945-1975 እ.አ.አ ጀምሮ የተለያዩ ስያሜዎችንና ሂደቶችን እየያዘ እደየወቅቱ ሊተገበር ችሏል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት መሰጠት የጀመረው በሃይማኖት ተቋማት (ክርስትና እና እስልምና ሃይማኖቶች) አማካኝነት ነበር። ከዚያም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሚሽነሪዎች ትምህርትን በተለይ መሰረተ ትምህርትን በማስፋፋት አስተዋፆኦ አድርገዋል። ከጊዜ በኋላ ከመደበኛው ትምህርት ጐን የጐልማሶች ትምህርት አስፈላጊነት ትከረት እያገኘ መምጣት ጀመረ። ስለሆነም መሰረተ ትምህርት ከባህላዊ ትምህርት ጋር ተያይዞ ይሰጥ ስለነበር ከመደበኛው ትምህርት የሚይተናነስ እድሜ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ይሁንና በአገራችን አዲስ ፌደራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ከተዘረጋ ወዲህ የተዘጋጀውን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት አድርጎ በተከታታይ በወጡት የትምህርት ዘርፍ ልማት ኘሮግራሞች ሕብረተሰቡን የትምህርት ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ የቆየ ቢሆንም በተለይ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ጀምሮ ትኩረት ተሰጥቶት በአዲስ አቀራርብ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እየተተገበረ ይገኛል።

ይሁን እንጂ በጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራም ሲሳተፉ ለነበሩ ወጣቶችና ጎልማሶች እንዲሁም በተለያየ መንገድ ማለትም በአብነት እና በመድራሳ ትምህርት ቤት ወዘተ---ሲማሩ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተገቢውን ምዘና ባለማግኘታቸው ቀጣይ ለሆነ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም ። እንዲሁም በአገሪቱ አማካኝ የትምህርት እድሜ **(Average years of Schooling)** አነስተኛ መሆን **(2.7 UNESCO 2017)** እና በአገሪቱ ከመደበኛው የትምህርት አቅርቦት ውጭ በተለያየ መንገድ መጻፍ ማንበብና ማስላት የሚችሉ ዜጎች መረጃ ቋት ( National Literacy Account )ውስጥ መካተት አልተቻለም ። ይህም በመሆኑም ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር መሰረታዊ ትምህርት ያገኙ ዜጎች ( Literacy Rate ) ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል።

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ለጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት አዲስ መዋቅር በመፍጠር ወደ ተግባር ተገብቷል ። በመሆኑም በጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የተሳተፉና በተለያየ መንገድ ማንበብ፤መጻፍ እና ማስላት የቻሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን "ትምህርት ለብርሀን' የሚል ምዘና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በመስጠት የወጣቶችንና ጎልማሶችን የማንበብ፤የመጻፍና የማስላት የብቃት ክህሎት ምዘናይካሄዳል።ተመዛኖች ባገኙት ውጤት መሰረት ዕውቅና እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ከዚህ በተጨማሪም የአገሪቱ አማካኝ የትምህርት እድሜና የተማረ የሰው ሀይል ቋት ማሳድግ/literacy account/ ያስችላል። ይህም በመሆኑም እንደፍላጎታቸው ለቀጣይ የትምህርትና ስልጠና ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያሰችላል ። ስለሆነም ይህን የትምህርት ለብርሀን ምዘና ማስተግበሪያ ማኑዋል ተዘጋጅቷል ።

## 3. ትምህርት ለብርሃን ምዘና አስፈላጊነት

ለበርካታ አመታት የጎልማሶችን የትምህርት ተደራሽነትና ጎልማሶች በሁለንተናዊ ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የተደረጉት ጥረቶች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም። በተለያዩ ጊዜያት የመሰረታዊ ትምህርት ብያኔዎች ፡ ይዘቶች ፡ አቀራረቦችና ንድፈ ሃሳቦች እያደጉና እየሰፉ መምጣታቸው ይታወቃል። በደፈናው የጎልማሶች ትምህርት ብለን የምንጠራው

ስፋቱና ጥልቀቱ በሰው ልጆች ህይወት ልክ የሰፋና ከኑሮና ከሰው ልጅ እድገት ጋር የሚለዋወጥ ነው። የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት በፈጣን የለውጥ ሂደት እንደመጓዙ መጠን የዘርፉን አድማስ በመረዳት ረገድ ክፍተቶች ሲስተዋሉ እንደነበር የማይካድ ሃቅ ነው።

የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ዘርፍ ከላይ የተገለጸውን የግንዛቤ ክፍተት በመረዳት መሰረታዊ ትምህርትን ወቅቱ በደረሰበት አለም አቀፍ ንድፈ ሃሳብ እንዲመረኮዝ ለማስቻል ትምህርት ለብርሃን የተሰኘ የምዘና መርሃ ግብር ነድፎ ወደ ተግባር ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛል። ትምህርት ለብርሃን ሰዎች ከትምህርት ቤቶች ወይም ከመማማሪያ ተቋማት ውጪ በተለያዩ መንገዶች የቀሰሙዋቸውን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የስሌትና የሕውት ክህሎት እውቀቶች እውቅና የሚሰጥና ለበለጠ የህይወት ዘመን ትምህርት/life long learnig/ ያላቸውን ተደራሽነት ለማስፋት ያለመ መርሃ ግብር ነው።

የትምህርት ለብርሃን ምዘነና መርሃ ግብር መነሻ ጽንሰ ሃሳቦች

- የጎልማሶች ህይወትና የስራ መስኮች መልከ ብዙ እንደመሆናቸው ጎልማሶች በመደበኛም ይሁን በኢ.መደበኛ የሚጠቀሙባቸው የመሰረተ ትምህርት አይነቶችም ብዝሀነት እንዳላቸው (Multiplicity of Literacies) የነበረው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን።
- የመሰረታዊ ትምህርትና ሰዎች ሃሳባቸውን ለሌሎች በማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸው የተግባቦት መንገዶች ፈርጀ ብዙ (Multimodal Literacies) ከመሆናቸውም ባሻገር የመሰረታዊ ትምህርት አካላት መሆናቸውን በበቂ ሁኔታ ያለመገንዘብና ትኩረት አለመሰጠቱ።
- በርካታ ምሁራን እንደሚከራከሩት በተለምዶ የምንጠቀምባቸው 'የመሃይማንና ከመሃይምነት የተላቀቁ' ሰዎች ሃሳባዊ ድንበሮች ክተጨባጭ ልምዶችና ከገሃዱ አለም እውነታዎች የራቁ በመሆናችው በመደበኛው የመሰረታዊ ትምህርት ተለምዶአዊ ምዘናዎች በማይምነት የምንፈርጃቸው ጎልማሶች ከመደበኛው ውጪ ባሉ (በመሰረታዊ ትምህርት እውቅና ሊቸራቸው የሚገቡ) የማንበብ ፤ መጻፍ ፤ እና የተለያዩ የተግባቦት ተግባራት ላይ ሲሳተፉ ማየት የተለመደ መሆኑ። ስለሆነም "የትምህርት ለብርሀን' ምዘናን በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በመተግበር የወጣቶችንና ጎልማሶችን መልከ ብዙ የማንበብ፤የመጻፍና የማስላት ክህሎት በመለየትና በሚያገኙት ውጤት መሰረት ዕውቅና በመስጠት ወደሚቀጥለው የትምህርትና ስልጠና ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ይሠራል። ፡ ይህ ማኑዋል የትምህርት ለብርሀን ምዘና መርሃ ግብርን ለማስተግበር የሚያገለግል ነው።

# 4. የመሰረታዊ ትምህርት ትርጉም

## 4.1. የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ትርጉም በኢትዮጵያ

አሁን ከአለንበት ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት በሀገራችን አንድ ወጥ የሆነ ለመሰረታዊ ትምህርት/ basic Literacy/ ተግባራዊ ትርጉም ማስቀመጥና በቀጣይ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በተመለከተ በተዘጋጅ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ሰነዶች መሰረት አድርጎ የሚከተለው ትረጓሜ ተሰጥቶታል ፡፡ መሰረታዊ ትምህርት/ **Literacy**/ ማለት የማንበብ፣ የመጻፍና የማስላት ክህሎትን ከዕለት ተዕለት ህይወት ጋር በማዛመድ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን አንድ ጎልማሳ መሰረታዊ ትምህርት አጠናቋል/ Literate/ የሚባለው በተለያየ መንገድ የማንበብ ፤የመጻፍና የማስላት ክህሎት የጨበጠ ወይም በጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፈው የተዘጋጀውን የአጥጋቢ የመማር ብቃት መለኪያ መሰረት የተቀመጠውን ዕውቀትና ክህሎት ሲጨብጡና በምዘና ሲረጋገጥ ነው፡፡

## 4.2. የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ትርጉም በዩኔስኮ

ዩኔስኮ የመሰረታዊ ትምህርትን ትርጓሜ ከማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ባሻገር የፕሮግራሙ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶች ማንበብ፣ መጻፍና ማስላትን ከዕለት ተዕለት የኑሮ ክንውኖቻቸው ጋር በማያያዝ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚያደርጉት ግንኙነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ እንደሚገባ አስቀምጧል፡

ስለዚህ የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ጽንሰ ሀሳብ በዓለም አቀፍ እይታ ጠቅለል ብሎ ሲቀመጥ ጎልማሶች የማንበብ፤የመጻፍና የማስላት ክህሎታቸውን ተጠቅመውና ፋላጎታቸውን መሰረት አድረገ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ተግባራዊ በሆነ መንገድ በመተግበር አቅማቸውን ሲያሳድጉና በማንኛው የልማት እንቅስቃሴ ተዋናኝ ሆነው ሲሳተፉና ይህም በተግባር የተመዘነ ሲሆን የመሰረታዊ ትምህርት ያጠናቀቁ ይባላል፡፡

# 5. የትምህርት ለብርሀን ምዘና ዓላማ

## 5.1. አጠቃላይ ዓላማ

**በተለያዩ መንገድ ማንበብ መጻፍና ማስለት ክህሎት ያዳበሩ ወጣቶችና ጎልማሶች ተገቢውን ምዘና እንዲያገኙ በማድረግና እዉቅና በመስጠት ለቀጣይ ሀገራዊ ልማት ብቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡**

## 5.2. ዝርዝር ዓላማ

- አማካኝ የትምህርት እድሜ( Average year of schooling) እና የተማሩ ሰዎች ቋት ( National Literacy Account ) ማሳደግ

- የወጣቶችንና ጎልማሶችን የማንበብ፣የመጻፍና የማስላት ክህሎት በመመዘን በሚያገኙት ውጤት መሰረት ዕውቅና መስጠት፣
- በምዘናው አጥጋቢ ውጤት ያስመዘገቡ ወጣቶችና ጎልማሶች እንደየፍላጎታቸው ወደሚቀጥለው የትምህርትና ስልጠና ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል
- የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራሞች ጥራትና ተገቢነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ቀጣይነቱን ማረጋገጥ

## 6. እነማን ይመዘናሉ ?

- **በምዘናው መሳትፍ የሚችሉት ከዚህ በፊት በተለያዩ ቋንቋዎች በተለያዩ መንገዶች የማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ክህሎት ያዳበሩ (ለምሳሌ ፡- በአብነት በመድረሳ ትምህርት እና በሌሎች መንገዶች የተሳተፉ ) ወጣቶችና ጎልማሶች ፤**
- **በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሀ-ግብር የተሳተፉ ወጣቶችና ጎልማሶች ይሆናሉ ።**

## 7. ምዘናው የሚያካትታቸው ይዘቶችና የምዘናው አይነት

### 7.1. በምዘናው የሚካተቱ ይዘቶች

የዚህ ምዘና ይዘት የሚመሰረተው ለጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት መርሀ-ግብር የተቀመጠውን አጥጋቢ የመማር ብቃት መለኪያ መሰረት አድርጎ በዋናነት ከዚህ በሚከተሉት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ይሆናል።

- የማንበብና መጻፍ ክህሎት
- መሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶች ክህሎት
- የክህሎት ልማት ( ለምሳሌ የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅና የጠፈጥሮ ሀብትን መከባከብ ወዘተ---)

### 7.2. የምዘናው ዓይነት

የሚሰጠው ምዘና በዋናነት ወረቀትና እርሳስን በመጠቀም ሆኖ ምርጫ፣ አዛምድና በአጫጭር ጹሁፍ መግለጽ ይሆናል።

### 7.3. ምዘናው የሚዘጋጅበትና የሚሰጥበት ቋንቋ

ምዘናው በሚካሄድባቸው በሁሉም ጣቢያዎች የተመዛኙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በአካባቢው በሚነገር ቋንቋ የሚዘጋጅና የሚሰጥ ይሆናል ።

## 8. ምዘናው የሚካሄድባቸው ቦታና ጊዜ

### 8.1. ምዘናው የሚካሄድባቸው ቦታ

ትምህርት ለብርሃን ምዘና በሁሉም የሀገሪቱ የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች በሚገኙ የጎልማሶች ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህር ቤቶች ፤የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከላትና ጤና ኬላዎች ሲሆኑ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ከህብረተሰቡ ጋር በመነጋገር የሚወሰን ይሆናል።

## 8.2. ምዘናው የሚሠጥበት ጊዜ

ምዘናው የሚሰጥበትን ጊዜ በሚመለከት የተመዛኞቹን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የአካባቢው የወረዳ ት/ጽ/ቤት በሚያወጣው መርሀ- ግብር መሰረት በዓመት ሁለት ጊዜ ወጥነት ባለው መልኩ በሁሉም ምዘና መስጫ ጣቢያዎች የሚከናወን ይሆናል።

# 9. የምዘናው አሰጣጥ፣ እርማትና ውጤት

## 9.1 የምዘና አሰጣጥ

የትምህርት ለብርሀን ምዘና በሚሰጥበት ጣቢያ የቅድመ ዝግጅቶችን ማለትም የመፈተኛ ክፍል አጽድቶ ማዘጋጀት፣ ምዘናው የሚሰጥበትን ቀንና ሰዓት የሚገልጽ ማስታወቂያ መለጠፍና ለተመዛኞች ማሳወቅ ፣ የምዘና ጥያቄዎችን ሚስጥራዊነታቸውን በጠበቀ ሁኔታና በበቂ መጠን ማባዛትና ሌሎችን የቅድመምዘና ስራዎች በዋናነት በአስተባበሪው የሚከናወን ይሆናል።

ምዘናው በሚሰጥበት ወቅት ለመመዘን ወደ ጣቢያው የሚመጡ ተመዛኞችን በትህትና በማስተናገድ መቀመጫቸውን እንዲይዙ ማድረግ፣ የተመዘኙ ሙሉ መረጃ መዝግቦ መያዝና ምዘናውን በአግባቡ ማካሄድ ። በመጨረሻም የተመዛኞችን የፈተና ወረቀት ቆጥሮና ከስም ዝርዝር ጋር በማመሳከር አረጋግጦ ለጣቢያ አስተባበሪው ያስረክባል ።

## 9.2 የምዘናው እርማት

የትምህርት ለብርሀን ምዘና እርማት በተመለከተ በዋናነት የመማማሪያ ጣቢያው አመቻቾች የሚያካሂዱት ሲሆኑ እንደአስፈላጊነቱ በጎ ፍቃደኞችን መጠቀም ይቻላል ።

## 9.3. የምዘናው ውጤት አሰጣጥ

የትምህርት ለብርሀን የምዘና ውጤት አሰጣጥን በተመለከተ ክንውኑ እንደሚከተለው ይሆናል።

- ማንበብ ከ 30%
- መጻፍ ከ 25%
- ማስላት ከ 30%
- ክህሎትልማት ከ 15%

# 10. የምስክር ወረቀት አሰጣጥና የሽግግር ሂደት የሚከናወንበት አግባብ

## 10.1. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፡-

- የምዘና ውጤትን መሰረት አድረጎ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በመደበኛው ትምህርት ያለውን አቻ የክፍል ደረጃ መሳተፍ የሚያስችል መሆኑን የሚገልጽ ይሆናል።

- የምስክር ወረቀቱ ህጋዊ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው በትምህርት ቤቱ ር/መምህር የተፈረመና የተቋሙ ማህተም ያረፈበት ይሆናል ።

## 10.2. የሽግግር ሂደት፡-

ምዘናውን ተመዝነው 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ያላቸውና የምስክር ወረቀት ያገኙ ተመዛኝ ወጣቶችና ጎልማሶች በመደበኛው ትምህርት ፕሮግራም 3ኛ ክፍል ካጠናቀቁት ጋር እቻ ይሆናሉ ። እንደፍላጎታቸውም የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ወይም ወደ ሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ገብተው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ።

# 11. በምዘና ሂደቱ ላይ የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 11.1. የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

- ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ቢሮዎች የሚካሄደውን ትምህርት ለብርሃን ምዘና ግንዛቤ ይፈጥራል
- በማዕከል በፕሮቶታይፕ መልክ የምዘና ጥያቄዎችን ያዘጋጃል፤ግንዛቤ ይፈጥራል ፤ያሰራጫል
- በማዕከል የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄ መነሻ በማድረግ ክልሎች በራሳቸው ቋንቋና እንደ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተተርጉሞ መዘጋጀቱን ይከታተላል
- ምዘናው በተቀመጠው ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎች መረጃ ከክልሎች ይሰበስባል፤ይተነትናል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ቢሮዎች ስለመተግበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል
- ሽግግሩ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጥነት ባለው መንገድ እንዲሆን የሙያ ድጋፍ ያደርጋል

## 11.2. የክልል/ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- ለሁሉም ዞኖች/ክፍለ ከተማ እና ወረዳዎች ትምህርት መምሪያና ትምህርት ጽ/ቤት የሚካሄደውን ትምህርት ለብርሃን ምዘና ግንዛቤ ይፈጥራል
- በማዕከል በፕሮቶታይፕ መልክ የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄዎችን ወደ ክልሉ /ከተማ አስተዳደሩ ቋንቋና ተጨባጭ ሁኔታ ይተረጉማል፤ግንዛቤ ይፈጥራል ፤ያሰራጫል
- በሁሉም የክልሉ ጣቢያዎች ምዘናው በተቀመጠው ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎች መረጃ ከዞኖች/ ክፍለከተማዎች ፤ወረዳዎች፤ ይሰበስባል ፤ይተነትናል የተጠቃለለ ሪፖርት ወደ ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ይልካል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱ በሁሉም ዞኖች/ ክፍለ ከተማዎች ፤ወረዳዎች፤ ስለመተግበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል

- ሽግግሩ በሁሉም ዞኖች/ ክፍለ ከተማዎች ፣ወረዳዎች፣  ወጥነት ባለው መንገድ እንዲሆን የሙያ ድጋፍ ያደርጋል

## 11.3. የዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

- በዞኑ ለሚገኙ ወረዳዎቸ ትምህርት ጽ/ቤት የሚካሄደውን ትምህርት ለብርሃን ምዘና ላይ ግንዛቤ ይፈጥራል
- በክልል በፕሮቶታይፕ መልክ የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄዎችን ወደ ዞኑ /ከተማ አስተዳደሩ ቋንቋና ተጨባጭ ሁኔታ ይተረጉማል፣ግንዛቤ ይፈጥራል ፣ያሰራጫል
- በዞኑ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎች ምዘናው በተቀመጠለት ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎች መረጃ ከወረዳዎች፣ ይሰበስባል ፣ይተነትናል የተጠቃለለ መረጃና ሪፖርት ለክልል ትምህርት ቢሮ ይልካል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱ ወረዳዎች፣ ስለመተግበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል
- ሽግግሩ በሁሉም ወረዳዎች፣ ወጥነት ባለው መንገድ እንዲሆን የሙያ ድጋፍ ያደርጋል

## 11.4. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤትተግባርና ኃላፊነት

- በወረዳው ለሚገኙ የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድና ለመዛኝ መምህራን ፣አመቻቾች፣በጎፋቃደኖች ፣ለግብርናና ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስለ ምዘናው አተገባባር ግንዛቤ ይፈጥራል ፣
- ጎልማሶችና ወጣቶች ለምዘና  እንዲመዘገቡም ለቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ አቅጣጫ ይሰጣል አፈጻጸሙንም ይከታተላል
- በዞን በፕሮቶታይፕ መልክ የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄዎችን ወደ ወረዳው ቋንቋና ተጨባጭ ሁኔታ ይተረጉማል፣ግንዛቤ ይፈጥራል ፣ያሰራጫል
- በሁሉም ቀበሌዎችና መማሪያያ ጣቢያዎች ምዘናው በተቀመጠው ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎች መረጃ ከምዘና መስጫ ጣቢያዎች ይሰበስባል ፣ይተነትናል የተጠቃለለ ሪፖርት ለዞን/ ለክልል ይልካል

## 11.5. የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

- ትምህርት ለብርሃን ምዘና ጠቀሜታ ለአካባቢው ማህበረሰብ መድረክ በመፍጠር ግንዛቤ ያስጨብጣል ፣ ለምዘናውም እንዲመዘገቡም ያደርጋል
- በቀበሌው ምዘና የሚሰጥባቸውን ጣቢያዎች ይለያል
- ለተመዛኝ ወጣቶችና ጎልማሶች የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ታትሞ  ለመማማሪያ ጣቢያዎች መድረሱን ያረጋግጣል

## 11.6. የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ተግባርና ኃላፊነት

    - ለምዘና የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን   ለጣቢያው ያሟላል

- ከአስተባበሪው ጋር በመሆን የተዘጋጀውን ፈተና ለተመዛኞች እንዲደርስ ያስተባብራል
- ለተመዛኝ ወጣቶችና ጎልማሶች የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት ያዘጋጃል
- በትምህርት ቤቱም ሆነ በዙሪያው በሚኖሩ የምዘና ጣቢያዎች የሚካሄደውን የምዘና ሂደት ከአስተባበሪው ጋር በመሆን ያስተባብራል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደት በበላይነት ይከታተላል ይቆጣጠራል

11.7. በመማመሪያ ጣቢያ ደረጃ የአስተባበሪው ተግባርና ኃላፊነት

- የምዘና ክፍሎች በተገቢው ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያደርጋል
- በምዘና ጣቢያው ለሚመዘኑ ጎልማሶች ስለምዘናው ጠቀሜታ እና ሂደት ግንዛቤ ያስጨብጣል
- በወረዳው በፕሮቶታይፕ መልክ የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄዎችን ወደ ቀበሌው ቋንቋና ተጨባጭ ሁኔታ ይተረጉማል፤ግንዛቤ ይፈጥራል ፤ ጥያቄውን ያዘጋጃል ምዘናው እንዲሰጥ ያደረጋል
- የጹሁፍ ምዘና ወረቀቶችን በአመቻቹ እንዲታረም ያደረጋል ፤ውጤቱን መዝግቦ ይይዛል
- የምዘና ውጤት መረጃ ተደራጅቶ እንዲያዝ ለአመቻቾች የቅርብ ክትትልና እገዛ ያደርጋል
- በምስክር ወረቀት አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጣቢያዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል
- የምዘናውን አጠቃላይ የሂደት ሪፖረት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል

11.8. የአመቻቾች ተግባርና ኃላፊነት

- የምዘና ክፍሎች ለተመዛኞች ምቹ የማድረግ ስራ ይሰራሉ
- በምዘና ጣቢያው ለሚመዘኑ ጎልማሶች ስለምዘናው ሂደት ገለጻ ያደርጋሉ
- ለምዘና ወደ ጣቢያው የሚመጡ ተመዛኞችን ምዝገባ ያደርጋሉ
- በጣቢያው በምዘና የተሳተፉትን አጠቃላይ መረጃ ይይዛሉ
- የተዘጋጀውን የምዘና ፈተና ለተመዛኞች ይሰጣል
- የምዘና ፈተናወን ያርማል
- የተመዛኞችን የምዘና ውጤት መረጃ ያደራጃል
- የምዘናውን አጠቃላይ የሂደት ሪፖረት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል

11.9. የተመዛኞች ተግባርና ኃላፊነት

- ተመዛኞች በጎልማሶች ትምህርትና በተለያየ መንገድ ማንበብ፤ መጻፍና ማስላት የሚችሉ መሆናቸውን አምነው በፍላጎታቸው ለመመዘን ይመዘገባሉ
- ተመዛኞች በፈተና ቀን ሰዓቱን አክብረው በመገኘት ምዘናቸውን/ፈተናቸውን በስራዓት ያከናውናሉ

12. የክትትልና ድጋፍ ስርዓት፡-

የትምህርት ለብርሃን ምዘና ተግባራዊ ለማድረግ በትምህርት ሴክተሩ በየደረጃው ባለው መዋቅር በቅድመ ምዘና ፣ በምዘናና ከምዘና ክንውን በኋላ በመድረክ ውይይት፤በስልክና በመስክ በመገኘት በቼክሊስት የተደገፈ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል ። በታዩ ክፍተቶች ላይ የመፍትሄ አቅጣጫ እየተሰጠ የምዘናው ተግባር ውጤታማ እንዲከናወን ይደረጋል። እንዲሁም በአፈጻጸሙ ላይ ግምገማ ይካሄዳል ግብረመልስም ለክልሎች ይላካል።